**Editor's Note**: I do not know who ጎማ እግሩ is, but the struggle he was engaged in and the many brave young Ethiopians he led may be very well known to me. He might have been in some command position when EPRDF finally entered Dessie. My own brother, Freedom Fighter Tekleabib Hagos (Tekleai) now deceased, was one of the fighters who came through that region and stationed in his place of birth, Dessie. This narration by ጎማ እግሩ is of particular significance and importance to me and to all, I hope. What we have in ጎማ እግሩ is a truly great Ethiopian, a patriot, a liberator, and someone with humility, and above all who had transcended petty ethnicism and envisioned the whole of Ethiopia with all of its people as a great single family of impressive history and in the process of transformation. The reason for posting ጎማ እግሩ's fabulous narrative here is to remind us all that there is something worth fighting for in our Ethiopia even when we are greatly discouraged, as I was due to the results of the 2010 National Elections. And when the dust settles, we are after all a band of brothers and sisters. Thank you ጎማ እግሩ for your sacrifice and faith in the Ethiopia we all love. **TH**

---

# ትክክለኛ የሆነ የተቃዋሚ ትግል እስከ አሁን አልታየም

በጎማ እግሩ [June 24, 2010]

*ይህን ታሪክ ዋርካ ውስጥ ላለው ወዳጄ በተለይም ደግሞ አገሩንና ህዝቡን በማገልገል ላይ የነበረ እንደ አንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ስሜቱ በደንብ ለሚረዳኝ የፃፍኩለት ሰው ነው ::*

*ጎማ እግሩ እናንተ እንደምታስቡት ወያኔ አይደለም ሆኖም አያውቅም ሊሆንም አይችልም :: ጎማ እግሩ በራሱ ዓለም የሚኖር የራሱ የሆነ ስሜት ያለው ግለሰብ ነው :: ጎማ እግሩ ድርጅትን እንደ እምነት አያምንም :: ግን የነፃነት ዓላማውን ለማሳካት ከኢህአደግ ጎን ተሰልፎ ያንን አርመኔ ደርግ ተዋግቷል :: ጎማ እግሩ ድሮም ድሃ ነው አሁንም ድሃ ነው :: ለየት የሚያደርገው ግን ደመኛ ጠላቱን ደርግን ተዋግቶ አባሮታል :: ከኢሀደግ ጋር የሚያገናኘውም ሆነ የሚያለያየው ነጥብ አለው :: ጎማ እግሩ ትክክለኛ የሆነ የተቃዋሚ ትግል እስከ አሁን አልታየም ብሎ ያምናል ::*

*ወደ ታሪኩ*

## Part 1

*ምንም እንኳ የተለያየ የፖለቲካ እምነት ቢኖረንም የአንድ አገር ልጆችና የአንድ ትውልድ ሰለባ ስለሆንን በዚያ ላይ መነጋገር እንችላለን በየ ነው ::*

*ከልጅነቴ ጀምሮ እስከመጨረሻዎች ጊዜያት ድረስ አንተ የምትለውን አባባልና አንተ የምታምነበትን አንድ ኢትዮጵያ አቋም ነበረኝ :: ያ ለሃገሩ መከበር ሲል በዱር በገደል ከአባቱ ጋር ሲዋጋ የነበረው አርበኛ አባቴ እንደ ባይተዋር እዚህ ግባ በማይባል የቀበሌ ካድሬ ተገድሎ ሲጣል ሶስት ታላላቅ (አንድ ወንድና ሁለት ሴቶች ) የወላድ አንጀት በሌላቸው ካድሬዎች በአይኔ በረቱ እያየሁ ሲደፋዋቸው እያየሁ ልቤ በሥርዓቱ እንጂ በምንም ላይ ቂም አልያዘም ነበር :: ይሁን ብየ ልኖር ስሞክርም ቀበሌ በ 1ኛ ተ .ቁ ለብሄራዊ ውትድርና አጨኝ :: ችግሬን ይሰሙኛል ብየ የአባቴ ጓደኛ የነበሩ አንድ ባለሥልጣን ጋ ሄድኩኝ :: አስበው እናቴ ንፁህ ኦሮሞ በአባቴ በኩል ደግሞ ወንድ አያቴ ትግሬ ሴት አያቴ ሸዋ አማራ :: አባቴም እኔም ኢትዮጵያዊነታችንን እንጂ ዘራችንን አስበነው አናውቅም :: ግን እንዳልኩህ የወንድ አያቴ ትግሬ ነበርና እሱም ልጁን የትግሬ ስም ሰጠው እኔ ደግሞ የዕብራይስጥ ስም*

ተሰጠኝ (ኮመን የኢትዮጵያ ስም ) ታድያ እዛ ባለሥልጣን ቢሮ በሄድኩበት ቀን መታወቂያ ስጠየቅ አውጥቼ ሰጠሁ :: ቀሪውን ምን ዕላሃለሁ የወያኔ ማዕከላዊ ኮሚቴ የያዙ ነው የመሰላቸው :: ማነው የላከህ ? አረ በፈጠራችሁ ሰው ለማናገር መጥቼ ነው ብል ማን ይስማኝ ? ከስድስት ወራት የማዕከላዊ ግርፋት በኃላ በነፃ ተሰናበትኩ :: እኔ በመታሰሬ ኑሮ ሆኖ እህቶቼ ተበለሻሽተው አየሁ አንጀቴ በገነ :: የትግራይ ዝርያ (በወያኔነት ) የኦሮሞ ዝርያ ያላቸው (በኦነግነት ) እስረኞች የታሰሩበትን ታሪክ ሲያስረዱኝ ዘርም እንደ ወንጀል ተቆጥሮ በሰው ልጅ ላይ ያደረሰውን መከራ ተመለከትኩኝ :: ስለ ሰሜን ተቃዋሚዎች የነበረኝ ግንዛቤም ተቀየረ :: ይህን መንግሥት መበቀል እንዳለብኝ ወሰንኩ አየር ወለድ ተቀጥሬ በም /መ /አ ተመረቅኩና ቤተሰብ ለመጠየቅ በሚል ሳቢያ ወደ ትግራይ (የአያቴ ዘመዶች ) ሄድኩኝ :: አልተመለስኩም :: ከ 8 አመት በኃላ በደብረዘይት መንገድ አዲስ አበባ በድል ተመለስኩ :: እናቴ ያንን አይታ ሞተች :: ሁለት እህቶቼም አረብ አገር ነበሩ በዚያው አውሮጳ መጡ እኔንና የቤቱን መጨረሻ ወንድሜን ባል ብለው አወጡን :: ኢህአደግን ከ 1988 ጀምሮ ተለይቸዋለሁ :: ግን የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነትና ደህንነት የሚጠቀምበትን ፖሊሲ አምኜ ተዋግቸለታለሁ :: ያ የተዋጋሁት ሰራዊት እንደኔ ተበዳይ መሆኑን አዋቃለሁ :: አከብረዋለሁ እከራከርለታለሁ :: አዲስ አበባ ስገባ የኮማንዶ ብርጌድ ምክትል አዛዥ ነበርኩ (እኛ ጋ ዘመቻ እንደሚባለው ነው ) ብዙውን የኢህአደግ ፕሮፖጋንዳ አልጋራም :: ግን ለኢትዮጵያ ከኢህአደግ የተሻለ ማን አለ በየ ስጠይቅ ማንም የለም :: ሁሉም ውሽታም ነው :: ያወራል እንጂ በጎን ከኛ ጋ ሲደራደር ነው የሚውለው :: አዲስ አበባ ከገባሁ ጀምሮ አጠራጣሪ ከሚባሉት አንዱ ስለነበርኩ ይህ ነው የተባለ ሥልጣን አልተሰጠኝም ግን የፀጥታን የደህንነት ኮሚቴን በማዋቀርም ይሁን የቤተመንግሥት ጥበቃ ብርጌድን በማሰልጠን እንዲሁም ማታ ማታ የፀጥታን ስምሪት በመቆጣጠር ላይ ነበርኩ :: እያንዳንዱን ስብሰባና ኮንፈረስ በሰልቃም እንዲካሄድ 24 ሰዓት ሰርቼ ነበር :: ክንፈና ሃሰን ሺፋ ለሥራ እንደሚፈልጉኝ ሁሉ ማየት እማይፈልጉት ሰው ቢኖር እኔን ነው ግን ያኔ አስፈልጋቸው ነበር :: የሚፈሩትን የአየር ወለድና ጥበቃ ብርጌድ እያንዳንዱን አውቃለሁ ስለዚህ እኔን ይፈልጉ ነበር :: ካለማወቅ የተነሳ ብዙ ጥፋት አድርገዋል :: ሳያጠፋ የሚያጠፋ መወንጀል የለበትም እያወቀ ትውልድ ያጠፋ በመለዮ ለባሹ ስም ህዝቡን የጨፈጨፈ :: ባንዴራውን ይዞ ቃለ መሃላ ፈፅሞ ያንን መሃላ አፍርሶ በአገር ሥም የኔንና የመላ ኢትዮጵያ ህዝብ ልጆች የፈጀውን :: ስለዚህ ጥፋታቸው ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ሄዶ አሁን ወዶ ምዕራባዊ የኮርፖሬት ዘረፋ ተሸጋግርሯል :: ይህ ደግሞ ፖለቲካ ሳይሆን ኮራፕሽን ነው :: ይህን ለመዋጋት ማን ተዘጋጅቷል ? ቢኖር እኔም እሰለፍ ነበር ግን ከጥላቻ ርቀን ቢያንስ ጠንካራና ደካማ ጎን ለይተን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ነገሮችን ብናይ ሁላችንም አንነጣጠልም :: የብሄረሰቦችን የራስብ በራስ ዕድል ከአሁን በኃላ ወደ ኃላ መመለስ አይቻልም ወደ ጥሩ መንፈስ ግን መመለስ እንችላለን ግን ሁላችንም ስናከብረው ነው ::

በ 1988 ሲያሰናብቱኝ በትህትና ነው ::
የመለዮ ለባሹ አባልም ባለውለታም ነኝ :: ሸሬ ሲደምሰስ የሻለቃ አዛዥ ሆኜ አብዛኛዎችን ጓደኞቼ እኔ ነኝ የማረኩዋቸው :: ተገቢውን እንክብካቤ እድርጌላቸዋለሁ :: በአካባቢህም አሉ ጠይቃቸው ::

## Part 2

ስለ አበረታች ደብዳቤህ ከልብ አመሰግናለሁ :: እንዳልከው ቀሪው ጊዜአችን በሰላም እንድናሳልፈው እግዚአብሄር ይርዳን ::

በኢህአደግ በኩል ያለውን ችግር አንተ እንዳስቀመጥከውነው በየ አላምንም :: እነሱን ከውጭ ስታያቸውና ከውስጥ ሆነህ ስታስባቸው አንድ አይደሉም :: በጀመሪያ ደረጃ ውስጣዊ ጥንካሬ አላቸው አይፍረከረኩም :: ችግሮች ሲመጡ ቶሎ አክሽን መውሰድ ይችላሉ እርስ በርስ ደግሞ አወነጃጀሉም :: ከመጀመሪያው ልጀምርልህ :: እነሱን ለመቀላቀል ስሄድ የአባቴ የአጎት ልጅ ቤት ነበር ያረፍኩት እና እነዚህ ወንበዴዎች ጋ ከምትሄድ ለምን ወደ ሱዳን ሄደህ አሜሪካ አትገባም ነበር ያለኝ :: ያኔ የሱ ልጆች በሱዳን በኩል ሄደው አሜሪካ ገብተው ነበር :: ለኔ ግን ስላልታየኝ ወደ ህወሓት እንዲልከኝ

አስረዳሁት እያዘነ ላከኝ :: አይወዳቸውም ነበር አሁንም አይወዳቸውም :: እዛ እንደደረስኩ ስለኔ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀባቸውም :: ከሶስት ወር ጥያቄ በኃላ ወደ ማስልጠኛ ጣቢያ (ግዴታ ነው ) እንድገባ ተደረገ :: ማሰልጠኛ ጣቢያ እንደደረስኩ አስልጣኞች ጋ ሆኜ ጠቃሚ እንደስልጣኝም እንደ አሰልጣኝም ለሶስት ወር ከጨርስኩ በኃላ የመቀሌ እስረኞችን የሚያወጣውን ዩኒት ከሌሎች ጋር በመሆን እንዳሰለጥን ኃላፊነት ተሰጠኝ :: የፕላኑ መሰረተ ኃሳብ ላይ አስፈላጊ የሆኑ መከራከሪያ ነጥብ እያነሳሁ እንዲሻሻሉም ተደረገ :: ልብ በል እንግዲህ መቀሌ መሆኑን የማውቀው ነገር የለም :: ሚሽኑን ብቻ ነው ስናጠና የነበረው :: በመጨረሻም ፕላቶን ኮማንደር ሆኜ የኔ ምድብ ቁልፍ እየሰበሩ እስረኝውን ለሚያውጡት የተኩስ ሽፋን መስጠት ነበር ኃላፊነቴ :: በአንድ በኔ ፕላቶን ውስጥ 3 አርፒጂ 47 ከ 36 ጥይት ጋር 3 ፒኪኤም መትረየስ ከ 3000 ጥይት ጋርና እያንዳንዱ ነፍስ ወከፍ ታጋይ 500 ጥይትና ሶስት ሶስት የእጅ ቦምብ ይዘን ነው የገባነው :: እስረኞች እንደምናወጣ ቀ :ቀኑ ሲስደርስ ነው ያወቅኩት :: ያኔ የተሰማኝን ደስታ ለመቆጣጠር ስላልቻልኩ አለቀስኩኝ :: ለምን አለቀስክ ተብየ በማዕከላዊ ኮሚቴ ተጠየቅኩ :: ቁስሌን የማድርቅበት አንዱ ሚሽን መሆኑንና የነበርኩበት ተመሳሳይ መሆኑን ስነግረው ማበረታቻ ሰጥቶኝ አሰናበተኝ :: ከልብ የሰራንለት ሚሽን ስለነበር 90% ተሳካልን :: የደርግ የመጀመሪያ ውድቀት በትግራይ ተበሰረ :: የህወሓት መሪዎች ተራ የሃይስኩል ተማሪዎችና የማሌን ሳይንስ ዛፍ ሥር ሆነው ያነበነቡ በአነጋገር የተሳሉ እንጂ አለም ዓቀፍ ሁኔታ አገናዝበው የኢትዮጵያን ህዝብ ስሜት ተረድተው የሚጓዙ አልነበሩም :: ሜዳ በነበሩበት ጊዜ ኃይለኛ ዲስፕሊን ነበራቸው :: በአጋጣሚ ትግርኛ የማልናገር የመጀመሪያው ታጋይ ሳልሆን አልቀርም :: በጆሮዬ ግን እሰማለሁ :: የሙያ ጉዳይ ሆኖ መሃል ስለነበርኩ ከመለስ ጀምሮ ሁሉንም አመራር እንደ ጓድ ነው የምናዋራቸው :: ከመለስ ጋር መገናኘት የለም እንጂ አጋጣሚ ካየኝ ጠርቶ እንደ ድሮው እየቀለደ ነው የሚያወራኝ :: ከዛ አብራኝ ያደገችው ማንነቴ ብቅ ስትል ሲያይዋት ግምገማ እያሉ ይጨፈጭፉኛል :: እኔም ሽንጤን ገትሬ እከራከራለሁ በመጨረሻ ልዩነቴ አስቀምጨ በድርጅቱ መርህ ለመስራት ተግባብቼ እንለያያለን :: ያኔ ይፈልጉኛል :: ለደርግ ያለኝ ጥላቻ ከነሱ በላይ ስለሚሆንባቸው አንዳንዴ ጥላቻን እንዳሰወግድና ዓላማ ላይ እንዳተኩር ይመክሩኛል :: የሚሰጠኝን ሥራ በአግባቡ ስለምፈፅም ያከብሩኛል :: በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሻምበል አዛዥነት ወደ ሻለቃ አዛዥነት ተሸጋገርኩ የሽሬ ጦርነት እንዳበቃ የምርኮኛውን መብት በማስጠብቅ ኃላፊነት ተመደብኩ :: ምርኮኛው ኢትዮጵያዊ ለሃገሩ የተሰለፈ ሰራዊት እንጂ ጠላት እንዳልሆነ ባለኝ አቅም አስረዳሁ ያም እንደመርህ ታይቶ ለፕሮፖጋንዳ ሲሉ በቪዲዮ እየቀረፁ አስራጩት ::

በወሎ ቀጠና ኃይለኛ የሜካናይዝድ ግብግብ ገጠምን :: የኔ ሻለቃ እልህ አስጨራሽ ሥራ ተሰጣት :: (የኔ ሻለቃ ከየክፍሉ በቅልጥፍናቸው የተመረጡ በኮማንዶ መጠነኛ ስልጠና የወሰዱ 550 አካባቢ የሚሆኑ 350 ወንድ 200 ሴት ኃይል ያለው ነበር ) 36 ሰዓት ከጀርባ በወጀራት ዞረን ከጀርባ በፍጥነት መግባት ነበረብን :: መንገድ ላይ ወደ 50 የሚሆኑ ሴቶች በድካም ቀነስንና ገባን ከ 2 ሰዓት የእጅ በጅ ዉጊያ በኃላ 4ኛ ሜካንይዝድን አፈረስነው አብዛኛውን ማረክነው :: በወንድምነት ስሜት እንጂ በጠላትነት ማየት ስለማይፈቀድ ሰራዊቱን እንደ ወገን ነበር የምንይዘው :: ይቀጥላል ሥራ ልሂድ

## Part 3

ከኣላማጣና ከቆቦ ውጊያ በኃላ ወልድያን ለመስበር በተደረገው ጥረት የጠበቅነውን ያህል ግፊት አልጠበቀንም እንም ወልድያን ወደ ግራ ጎን በመተው ከደብረታቦር የሚመጣውን መንገድ በመዝጋት ወደ ጢጣ ስንቀሳቀስ ውጫሌ ላይ ቆሰልኩኝ :: ቀላል ስለነበር ከሁለት ሳምንት በኃላ ህክምና በኃላ ተመለስኩኝ ጢጣ ለመግባት ኃይቅ ዞርያ ተራራዎች ላይ ከፍተኛ ትንቅንቅ ተደረገ :: በዚህ መሃል ላይ ደርግ በሞራል ተነክቶ ያለ ጦርነት መፍረክረክ ሲጀምር አሰብ ኮምቦልቻ መንገድን ለመዝጋት አንድ ብርጌድ ተንቀሳቀሰ የዚህም ብርጌድ ምክትል አዛዥ ሆንኩ ከዚያ በኃላ ደጋውን እየለቀቅኩ ወደ አሰብ መነገድና አዋሽ ተንቀሳቀስኩ አዋሽ አርባን በ 25 ደቂቃ ጦርነት ተቆጣጠረነው ከዚያ ናዝሬት ከዚያ ምን ልበልህ አ /አ በገባሁ በሶስተኛ ቀን ከሰራዊቱ ተሰናብቼ በጥበቃ ሥር እንድሆን ተደረገ :: ጥበቃው ፖሊስ ሴኩሪቲንና የዞን ሰላም ማስከበሪያ ፅ /ቤትን ይመለከታል :: አባቴን የገደለውን

የከፈተኛ አብዮት ሊ /መንበር አግኝቼው በህመም ይሰቃይ ስለነበር ምንም ላደርገው አልቻልኩም :: የፈጣሪ ፍርድ እንደሚሻልም ስለማውቅ ያን ሰው መበቀል ተገቢ እንዳልሆነና እንድያውም ወደ ኬንያ መሄድ እፈልጋለሁ እና እርዳኝ ብሎ ልኬው አሁን አውስትራሊያ አለ :: በኃላም የአባቴን አሟሟት ምክንያቱን ፈልጌ ሳየው ታሪኩ ረጅም ነው :: ለካንስ አባቴ የደርግ አባል ከነበረው ከሻለቃ ሲሳይ ሄብቴ ጋር ወዳጅ ስለነበር ነው :: እህቶቼም ይሁን ወንድሞቼ የኢህአፓ አባል እንደነበሩ አረጋግጫለሁ ::

ወደ ህወሃት ሰዎች ስወስድህ ግን በአብዛኛው እንደሚወራው ፀረ -ኢትዮጵያ አቋም ያላቸው አይደሉም :: ሜዳ እያሉ በስሜት የሚጓዙና አስተሳሰባቸው ቁንፅል ነው :: አብዛኛው ታጋይ የኤርትራ መገንጠል አይደግፍም ነበር ግን ዋናው አትኩሮ የነበረው ደርግን የመጣል ነበር :: በኃላም በወታደራዊ ድል ስካር የሚሆኑት ጠፍቷቸው ነበር :: አዲስ አበባን እንይዛለን የሚለው ግምት የዳበረው ደብረ ታቦርን መያዝ ስንጀምር ነው :: ከዚያም አዲስ አበባ ከተያዘ በኃላ ብዙ ስህተቶች ይፈፀሙ ነበር :: እንዲያውም ኮማንድ ኔትዎርኩ ዝብርቅርቅ ብሎ ነበር :: ሁሉም ያሻውን ይፈፅማል ነገሮችን ለመቆጣጠር አልተቻለም ነበር :: የነሱ ጥንካሬአቸው ግን እርስ በርስ አይወነጃጀሉም (እንደ ተቃዋሚው ) ለድርጅቱ ስራ ሲባል የተፈፀመው ጥፋት በሙሉ ይቅርታ አለው :: ይቅርታ የሌለው ነገር ቢኖር ለውጭ ሰው አሳልፈህ መስጠትና ከድርጅቱ ፖሊሲ ጋር የሚፅረር ሥራ መስራት ነው :: ባይገርምህ ከተከዜ ጫካ የመጣው የህወሃት ቢሮክራሲ ሽገር ግብቶ ከ 4 አመት በኃላ ሌላ ባህርይ ያዘ :: የገባን ሰሞን አንዱ የህወሃት ማዕከላዊ ኮሚቴ አንድ ቀን ቢሮ ጠራኝና እኔ ይህ ወንበር አልመቸኝ አለ ትግራይ ቢመድቡኝ ይሻለኛል አለኝ :: ለምን ስለው ነገሩ እንደዚህ የሚቀጥል ከሆነ እኛስ ከደርግ በምን ተሻልን አለኝ :: ይህን ያለበት ምክንያት ያ ሁሉም ሰው በጓዳዊነት ስም አብሮ ሲበላ ሲጨፍ የነበረ ታጋይ ግማሹ አጃቢ ግማሹ ደግሞ ታጃቢ ግማሹ ቺቫዝ ሬግል ሲጠጣ ግማሹ ደግሞ የቢራ አጥቶ ሲቸገር ስለተመለከተ ነው :: ባለቾኝ አቅሚቲ ትላንት ዛሬ አይደለም ሁሉም ነገር እንደነበረው አይሆንም አንተም እስከምትችለው ድረስ ልክ ነው የምትለውን ነገር እየሰራህ እለፍ አልኩት :: ያ ሰው አሁን እኛ ጋ በስደት አለ :: ይቀጥላል

## Part 4

በአጠቃላይ ከላይ እንደገለፅኩልህ አዲስ አበባ ከገባን ጊዜ ጀምሮ "ተፈላጊ ሆንኩ ":: ተፈላጊ ስልህ በደንብ እንደሚገባህ ይሰማኛል :: አንድም ከነሱ የተሻለ የአዲስ አበባና የነበረውን መንግሥት ባህርይ አውቃለሁ :: በተለይም በፀጥታና በኮማንዶ ሰርክል ውስጥ የነበሩትን ሰዎች የእያንዳንዱን ግለሰብ ጥንካሬና ድክመት ስለማውቅ ከዚያም ደግሞ በሥራ ላይ ከነበረው የፖሊስና ሲቪል መንግስታዊ ተቋሞች ለመግባባት ብዙ እንደማይፈጅብኝ ስለተገነዘቡ ነው አዲስ አበባ እንዲሆን የተደረገው :: ለራሴም አስደንጋጭና ያላሰብኩት ነገር የሆነብኝ የአዲስ አበባ ፀጥታን በሚመለከት ማማከሩ በሙሉ እኔ ላይ ተጣለ :: ተጠሪነቴ ለብርጌድ አዛዥና ለክ /ጦር የነበርኩት ሰውዬ ከኢህአደግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ጋር ለመሰብሰብም በቃሁ :: ይህ ነው የሚባል 'ታይትል ' የለኝም ግን በፖሊስ ኮምሽኑ አቶ ሃሰን ሺፋና በደህንነት ኃላፊው አቶ ክንፈ ዙርያ ሆኜ የመንግስታዊና ህዝባዊ ድርጅቶች ጥበቃ ከዚያ በተጨማሪ ጠባሴ በነበረው የኮማንዶ ማስልጠኛ ት /ቤት የሚሰለጥኑትን የቤተመንግስት ጠባቂዎች መከታተል ነበረ ስራዬ :: ኦነግ ራሱን ከምርጫ ሲያገልልና የትጥቅ ትግሉን እንደ አማራጭ ሲያስቀምጥ ኦፒዲኦን ማጠናከሩ አስፈላጊ ስለነበርና በኦርሚያ ይኖሩ የነበሩ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ላይ ግፍ ይፈፀም ስለ ነበር ወደ ኦሮሚያ ክልል ሄጄ ይህን ነገር እንድቆጣጠር ተመደብኩ :: እንግዲህ ልብ በል በህወሓት ታጋዮችና ኦፒዲኦን በመሰረቱት ታጋዮች መካከል ያለውን የሥነ -ልቦናን የፖለቲካ መሰረታዊ ልዩነት :: ከምርኮኛነት ወይንም ከ 10አለቃነት ወደ አገር መሪነት :: እኔ ራሴ የማረኩት መ /አ የኦፒዲአ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሆኖ በፖለቲካ ስልጣኑ የኔ አለቃ ሆኖ እኔ ደግሞ የእሱን ውስጠ ደካማነት ስለማውቅ የሚኖረኝ ስሜት ...... የኢህአደግ ዓላማና ተግባር ለየቅል ሆነ :: ጭራሽ በአካባቢው ተፀጥታ ኃይሎች እንድጠላ ተደረገ :: አስብ እንግዲህ ትግራይ ጎጃም ጎንደር ያለው ገበሬ ከመታጠቁ በፊት በፖለቲካው አቋም ላይ አምኖ ነው :: ከአንድና ከሁለት ክፍለሃገር ውስጥ

ሲንቀሳቀስ የነበረ ኃይል 14ቱም ክ /ሃገራት ሲዘራ በኦታውን ለመሸፈን የነበረውን ችግር ተረዳ :: ስለዚህ የተገኘውን እደግፋለሁ ያለውን ነበር ኢህአደግ ያስታጠቀው :: ያ መዘዝ ነው ደግሞ ህዝቡን ቅር ያሰኘው :: ዓላማው ሳይሆን አፈፃፀሙ :: ማንም ይሁን ማንም በዚያን ወቅት ለመቆጣጠር ያስቸግር ነበር :: ጥፋቱ ታድያ የነበረኡትን የሃገሪቱን የመከላከያ ተቋሞች ከማፍረስ ይልቅ እንዳለ የውስጥ ጥገና አድርጎ ኃላፊነቱን መስጠት ሲቻል በራሳቸው የማይተማመኑት የኢህአደግ ኃይሎች እንዲበተን አስደረጉ :: ውጤቱም የከፋ ሆነ :: ይህን አስተያየት ስብሰባ ላይ ስስጥ እኔ ራሴ የሰራዊቱ አባል ስለነበርኩ አንደ ሲምፐታይዘር ነበር የታየሁት :: ግን በድምፅ ብልጫ የምንጓዝበት ጊዜ ስለነበር ምንም ማድረግ አልተቻለም ::

በተቋሚዎች እንደሚወራው ተወውና በውስጥ አውቂነቴ አንድ ነገር ልበልህ :: ሁሉም ታጋዮች ኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲ ፍትህ እኩልነት በዋናነት ደረጃ ደግሞ የብሄር ብሄረሰቦች እክልነት ይኖራል የሚል ራዕይ ነበራቸው :: አስቸጋሪውና ሁሉንም , ያበላሸው ግን የችሎታ ማነስና ሁሉንም በጠላትነት የማየት አባዜ አላማቸውን ቀይሶታል :: ወደ ተቃዋሚዎችም ስትመጣ ጥላቻን ያዘለ መልዕክት ከማስተላለፍ አልፈው ወጥ የሆነ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ አልቻሉም :: እንደ ህወሓት ባሉ ድርጅቶች ከምንም በፊት የድርጅትህን ጥንካሬ እንድትፈትሽ ጥንቃቄ ይደረጋል :: የኛ ተቃዋሚዎች ግን "ከማውራት " የዘለለ እንቅስቃሴ አያደርጉም :: የፖለቲካ ትግል ትዕግሥትና ስልት ያስፈልገዋል :: ብልሃትና ዘዴ ደግሞ ወሳኝ ነው :: ውስጣዊ ጥንካሬ የሌለው ድርጅት መስርቶ ትግል መጀመር ጀብደኝነት ነው :: ለምሣሌ ኢህአደግን እርቃኑን ማስቀረት ከፍለክ በመርህ ደረጃ የብሄር ብሄሰሰቦችን መብት እያስከበርክ ህግመንግሥቱን እንደምታከብር እየጠቀስክ ያለውን ሥርዓት ዝቅጠት እያስረዳህ ስትጓዝ እንኳንስ ሌላው ኢትዮጵያዊ የኢህአደግ አባላትም ሊደግፉህና ለውጥ ማምጣት ትችላለህ :: አንዴ የፖለቲካ ስልጣኑን ከያዝክ በኃላ ደግሞ ከህዝብ ጋር እየተማከርክ ታስተካክላለህ :: ግን አሁን ያለው ትግል ኢህአደግን እንደ ጠላት በማስቀመጥ የምትፈረጅ ከሆነ ሁሉም በኢህአደግ ዙርያ ያሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ለኢህደግ ያላቸው ታማኝነት እየጠነከረ ይሄዳል ;; ኢህአደግም ስልጣን የማስረከቡ ፍላጎቱ ይቀንሳል :: ማን መታሰርናን መገደልን የሚፈልግ አለ ?

በጎማ እግሩ [June 24, 2010]
Source: WARKA